

**በፕሬዘደንት**
**ሔንሪ ቢ. አይሪንግ**
የቀዳሚ አመራር
የመጀመሪያ አማካሪ

# ወንጌልን ልብ ለልብ መካፈል

እግዚአብሔር ወንጌሉን ለማካፈል ፈቃደኛ በሆኑ አገልጋዮቹ መንገድ ፊት የተዘጋጁ ሰዎችን ያስቀምጣል። እናንተም ይህ በህይወታችሁ ደርሶባችሗል። ድግግሞሹ እንደ አዕምሮአችሁ እና ልባችሁ መዘጋጀት ይወሰናል።

ወንጌልን ለመቀበል ከተዘጋጀ ሰው ጋር ለመገናኘት ዘወትር የሚጸልይ አንድ ጓደኛ አለኝ። መፅሐፈ ሞርሞንን ሁልጊዜም ይዞ ይሄድ ነበር። አጭር ጉዞ ከማድረጉ በፊት ባለው ምሽት፣ መፅሀፉን ሳይሆን በራሪ ወረቀት ይዞ ለመሄድ ወሰነ። ነገር ግን ለመውጣት ሲዘጋጅ፣ “መፅሐፈ ሞርሞንን ይዘህ ሂድ” የሚል የመንፈስ ሹክሹክቻ መጣለት። በሻንጣው ውስጥ አንድ አስቀመጠ።

በጉዞው ጊዜ የሚያውቃት አንድ ሴት በአጠገቡ ስትቀመጥ፣ “እርሷ ትሆን?” ብሎ አሰበ። ከጉዞ በሚመለስበት ጊዜም አብራው ተጓዘች። “ስለወንጌሉ ለመነጋገር እንዴት መጀመር እችላለሁ?” እያለ አሰበ።

እርሷ ግን “ለቤተክርስትያንህ አስራት ትከፍላለህ፣ አይደለ ምን?” አለችው። እርሱም እከፍላለሁ አለ። ለቤተክርስቲያኔ አስራት መክፈል ቢኖርብኝም አልከፈልኩም አለች። እናም “ስለመፅሐፈ ሞርሞን ምን ልትነግረኝ ትችላለህ?” ብላ ጠየቀችው።

እርሱም መፅሐፉ ከቅዱሳት መጻህፍት አንዱ፣ ሌላኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር፣ እና በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ተተረጎመ ገለጸላት። ለማወቅ የምትፈልግ ስለመሰለች ወደ ሻንጣው እጁን አስገብቶ “ይህን መፅሐፍ ይጄው እንድመጣ ስሜት ተሰምቶኝ ነበር” አለ። “ይህም ለአንቺ መሆኑን ነው የማስበው።”

እርሷም መጽሀፉን ማንበብ ጀመረች። ሲለያዩም፣ “እኔ እና አንተ ስለእዚህ ተጨማሪ እንነጋገርበታለን” አለችው።

ጓደኛዬ ያላወቀው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር አውቆት የነበረው ቢኖር ቤተክርስቲያን እየፈአገች ነበር። እርሷ ጓደኛዬን እንደተመለከተች እና ቤተክርሲያኑ ለምን ደስተኛ እንዳደረገው ትገረም እንደነበር እግዚአብሔር አውቆ ነበር። ስለመፅሐፈ ሞርሞን እንደምትጠይቅ እና በወንጌል መልእክተኞች ለመማር ፈቃደኛ እንደምትሆንም እግዚአብሔር አውቆ ነበር። ተዘጋጅታ ነበር። ጓዳኛዬም ተዘጋጅቶ ነበር። እኔ እና እናንተም ለመዘጋጀት እንችላለን።

ለመዘጋጀት የሚያስፈልገንም በአዕምሮአችን እና በልባችን ውስጥ ነው። ሴቷ ስለመፅሐፈ ሞርሞን፣ በጌታ በዳግም ስለተመለሰው ቤተክርስቲያን፣ እና ለእግዚአብሔር አስራት ስለመክፈል ትእዛዝ ሰምታ እና አስታውሳ ነበር። በልቧም የእውነት ምስክርነት ስሜት መጀመሩን ተሰምትዋታል።

ጌታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአዕምሮአችን እና በልባችን እውነትን እንደሚገልጥ ተናግሯል (ት. እና ቃ. 8:2 ተመልከቱ)። የምትገናኟቸው ብዙዎቹ ሰዎች የዚህ ዝግጅት ጅማሬ ነበራቸው። ስለእግዚአብሔር እና ስለቃሉ ሰምተዋል ወይም አንብበዋል። ልባቸው ለስላሳ ከሆነ፣ ግልጽ ባይሆንም ኣንኳ የእውነት ማረጋገጫ ስሜት ነበራቸው።

ያችም ሴት ተዘጋጅታ ነበር። መፅሐፈ ሞርሞኑን ያጠናው

ጓደኛዬም ተዘጋጅቶ ነበር። ይህም እውነት እንደሆነ ተሰምቶታል፣ እናም መፅሐፉን ይዞ እንዲሄድ ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን መመሪያ ተገንዝቧል። በአዕምሮው እና በልቡ ተዘጋጅቶ ነበር።

እግዚአብሔር ዳግም ስለተመለሰው ወንጌል ያላችሁን ምስክርነት እንዲቀበሉ ሰዎችን እያዘጋጀ ነው። የእናንተን እምነት እናም ከዚያም ለእናንተ እና ለምትወዷቸው ከሁሉም በላይ ውድ የሆነላችሁን ነገር ያለፍርሀት የማካፈልን ተግባር ይጠብቅባችኋል።

በየቀኑ አዕምሮአችሁን በወንጌል እውነት በመሙላት ለማካፈል ተዘጋጁ። ትእዛዛትን ስትጠብቁ እና ቃል ኪዳናችሁን ስታከብሩ፣ የመንፈስ ምስክርነት እና በተጨማሪ ም ለእናንተ እና ለምትገናኟቸው ያለውን የአዳኝ ፍቅር ይሰማችኋል።

ድርሻችሁን ከተወጣችሑ፣ ከእናንተ ወደ እነርሱ የሚቀርበውን የልብ ለልብ ምስክርነታችሁን ለመስማት የተዘጋጁ ሰዎችን የማግኘት አስደሳች አጋጣሚዎችን ይበልጥ ታገኛላችሁ።

---

### ከዚህ መልእክት ማስተማር።

የእራስን ምስክርነት የሚጠናከርበትን መንገድ ፕሬዘደንት አይሪንግ የተናገሩትን ከመጨረሻ አንቀጽ በፊት ያለውን አንቀጽ መልእክቱን ከቤተሰብ ጋር ለማንበብ እና ለመወያየት ተመልከት። ወንጌልን ስታካፍሉ ምስክርነታችሁን የማካፈል አስፈላጊነትን ከቤተሰብ ጋር ተወያዩበት። በቤተሰብ ወስጥ ያሉ ልጆችም ለጓደኞቻቸው እንዴት ምስክርነታቸውን ማካፈል እንደሚችሉ ለማሳየት መለማመድ ይጠቅማቸዋል።

## ወጣት

### የሚናገሩትን ማወቅ

ወንጌልን ከሌሎች ጋር ለማካፈል በቂ እውቀት እንደሌላችሑ ከተሰማችሁ፣ ከቅዱሳት መጻህፍት ባሉት የተስፋ ቃላት ተፅናኑ፥

“ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ እነዚህ ህዝቦች ድምጾቻችሁን ከፍ አድርጉ፤ በልባችሁ የምጨምረውን ሀሳብ ተናገሩ፣ እና በሰዎችም ፊት አታፍሩም፤

የምትናገሩትን በዚያች ሰዓት፣ አዎን፣ በዚያች ጊዜም፣ ምን እንደ ምትናገሩ ይሰጣችኋልና።” (ት. እና ቃ.100፥5–6)።

“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።” (ዮሀንስ 14፥26)

እነዚህ ታላቅ የተስፋ ቃላት ናቸው፣ ነገር ግን እነዚህን ለማግኘት የእኛን ፋንታ ማከናወን አለብን። በእዚህ መልእክት ውስጥ ፕሬዘደንት አይሪንግ እንዳስተማሩን፥ “[ወንጌሉን] በየቀኑ አዕምሮአችሁን በወንጌሉ እውነት በመሙላት ለማካፈል ተዘጋጁ።” አዕምሮአችሁን በወንጌል እውነት ለመሙላት ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

## ልጆች

### ለማካፈል መዘጋጀት

ፕሬዘደንት አይሪንግ ወንጌልን ለማካፍል አስፈላጊ የሆነ መንገድ አዕምሮአችንን በወንጌል እውነት መሙላት ነው ብለዋል። ለማካፈል ለመዘጋጀት ማድረግ የምትችሏቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቱ በህግ የተጠበቀ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/11 (እ.ኤ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/11 (እ.ኤ.አ)
*First Presidency Message, September 2012* (እ.አ.አ) ትርጉም። Amharic። 10369 506

# ልዩ ፍላጎቶች እና እርዳታ የተሰጠበት

*ይህን መልዕክት በጸሎት መንፈስ አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ንቁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው።*

**እምነት, ቤተሰብ, እርዳታ**

ፕሬዚደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን እንዳሉት፣ “እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዘወትር ይገኛሉ እናም እያንዳንዳችን ሰውን ለመርዳት አንድ ነገር ለማድረግ እንችላለን ሌሎችን በማገልገል እራሳችንን ካልረሳን በስተቀር፣ በህይወታችንም ውስጥ ያለው አላማ ያነሰ ይሆናል።”[1]

የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት አስተማሪዎች እንደመሆናችን መጠን፣ የምንጎበኛትን እያንዳንዷን እህት ማወቅ እና ማፍቀር እንችላለን። ለምንጎበኛቸው ሰዎች የምናደርገው አገልግሎት ለእነርሱ ካለን ፍቅር ይመነጫል (ዮሀንስ 13፥34–35 ተመልከቱ)።

እርዳታ በሚያስፈልግበት ጊዜ ለመስጠት እንችል ዘንድ እንዴት የእህቶቻችንን መንፈሳዊ እና ስጋዊ ፍላጎት ማወቅ እንችላለን? የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት አስተማሪ እንደመሆናችን መጠን፣ ስለ ምንጎበኛቸው ሰዎች ስንጸልይ፤ መንፈሳዊ ምሪትን የማግኘት መብት አለን።

ከምንጎበኛቸው እህቶች ጋር ቋሚ ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ ነው። የግል ጉብኝቶች፣ የስልክ ጥሪዎች፣ የማበረታቻ ማስታወሻ፣ ኢሜል መላክ፣ ከእርሷ ጋር መቀመጥ፣ ከልብ የመነጨ ሙገሳ መስጠት፣ በቤተክርስቲያንም እርሷን ማነጋገር፣ በበሽታ ወይም በችግር ጊዜም እርሷን መርዳት፣ እና ሌሎች የአገልግሎት ስራዎች በሙሉ እርስ በርስ እንድንጠባበቅ እና እንድንጠነካከር ይረዱናል።[2]

የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት አስተማሪዎች፤ የእህቶችን ደህንነት፣ ምን እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው፣ እና ምን አገልግሎት እንደተሰጣቸው ዘገባ እንዲያቀርቡም ተጠይቀዋል። እንደዚህ አይነት ዘገባዎች እና ለእህቶቻችን የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ደቀ መዛሙርትነታችንን እንድናሳይ ይረዱናል።[3]

### ከቅዱሳት መጻህፍት

ዮሀንስ 10፥14–16፤ 3 ኔፊ 17፥7፣ 9፤ ሞሮኒ 6፥3–4

### ከታሪካችን

እርስ በራስ ማገልገል ሁልጊዜም የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት ትምህርት ዋና ክፍል ነው። ቀጣይነት ባለው አገልግሎት፤ በየወር ከመጎብኘት በላይ የሆነ ደግነትን እና ጓደኝነትን እናመጣለን። መቆርቆራችን ነው የሚቆጠረው።

13ኛዋ የሴቶች መረዳጃ ማህበር አጠቃላይ ፕሬዘደንት የነበሩት ሜሪ ኤለን ስሙት እንዳሉት፣ “የኔ ፍላጎት የስልክ ጥሪን ወይም በአመት ሶስት ጊዜ ወይም በየወሩ ስለሚደረገው ጉብኝት ማሰብ እንዲያቆሙ ልለምናቸው እፈልጋለሁ።” እንዲህም ጠይቀውናል፣ “በዛ ፋንታ ሩህሩህ የሆኑትን ነፍሳት በመንከባከብ ላይ አተኩሩ።”[4]

ፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል [1895–1985 (እ.ኤ.አ)] እንዳስተማሩት፣ “በእርስቱ ወስጥ እርስ በራስ ማገልገል በጣም አስፈላጊ ነው።” ነገር ግን ሁሉም አገልግሎቶች በጀግንነት የሚደረጉ እንዳልሆኑም አውቀዋል። እንዲህም አሉ፣ “ብዙውን ጊዜ፣ አገልግሎታችን ቀላል በሆነ ማበረታቻ ወይም ስጦታ የሚከናወን ነው. . . ነገር ግን ትንሽ ቢሆንም በጥንቃቄ በተደረገ ስራ ምክንያት የሚመጣው ውጤት እንዴት አስገራሚ ነው።”[5]

**ማስታወሻዎች**

1. ቶማስ ኤስ. ሞንሰን፣ “What Have I Done for Someone Today?” *Liahona*፣ ህዳር 2009፣ 85።
2. *Handbook 2: Administering the Church* (2010)፣ 9.5.1 ተመልከቱ።
3. *Handbook 2*፣ 9.5.4 ተመልከቱ።
4. ሜሪ ኤለን ስሙት፣ በ*Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society* ውስጥ (2011)፣ 117።
5. *Teachings of Presidents of the Church: Spencer W. Kimball* (2006)፣ 82።

### *ምን ማድረግ እችላለሁ?*

**1.** እንድጠብቃት ለተመደብኩላት ለእያንዳንዷ እህት፤ መንፈሳዊ እና ስጋዊ ፍላጎት መልስ ለመስጠት እንዴት እንደምችል ለማወቅ የግል ተነሳሽነትን ፈልጌአለሁን?

**2.** የምጠብቃቸው እህቶች ስለእነርሱ እና ስለቤተሰቦቻቸው እንደምጨነቅላቸው እንዴት ያውቃሉ?

ለበለጠ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org ሂዱ።

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቱ በህግ የተጠበቀ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.ኤ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.ኤ.አ) *Visiting Teaching Message, September 2012* (እ.ኤ.አ) ትርጉም። Amharic። 10369 506